መልእክት ሰባት

**መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት መናገሩ፣**
**የዳዊት መክፈቻ ያለው ማንነት**
**እና ከድል ነሺዎቹ ጋር እራት የሚበላው ማንነት**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ራእ. 3፥7-22

**I. በራእይ 2 እና 3 ክርስቶስ ለአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የሚናገረው መንፈስ ነው፡-**

ሀ. በራእይ 2 እና 3 በእያንዳንዱ መልእክት መጀመሪያ ላይ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት በቅደም ተከተል የተናገረው የማይወሰነው፣ የሕይወት-ለቃቂው፣ ሰባት እጥፍ ያየለው፣ የእስትንፋሳዊው ክርስቶስ ንግግር (2፥1፣ 8፣ 12፣ 18፤ 3፥1፣ 7፣ 14) ሰባት እጥፍ ያየለው፣ ሁሉን ያካተተው ሕይወት የሚሰጠው መንፈስ በእያንዳንዱ መልእክት መጨረሻ ላይ ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ አጽናፍ-ዓለማዊ በሆነ መልኩ የተናገረው ንግግር ይሆናል (2፥7፣ 11፣ 17፣ 29፤ 3፥6፣ 13፣ 22)።

ለ. ስለዚህ፣ የሚናገረው ክርስቶስ፣ የሚናገረው መንፈስ፣ ለአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የሚናገረው መንፈስ ይሆናል፤ ክርስቶስ ለአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ይናገራል፣ መንፈስ ደግሞ ለአጽናፍ ዓለማዊው አካል ይናገራል።

ሐ. ይህ የሚያመለክተው መንፈስ ጌታ መሆኑንና ጌታ መንፈስ መሆኑን ብቻ ሳይሆን፣ በ 1፥4 ላይ ሰባት እጥፍ ባየለው መንፈስ እንደተመለከተው በቤተ ክርስቲያን ዝቅጠት ጨለማ፣ መንፈስ እጅግ ወሳኝ ለመሆኑም አጽንኦት ይሰጣል።

መ. በራእይ 2 እና 3 ያሉት ሰባት መልእክቶች በጌታ ኢየሱስ የተነገሩ ቃሎች ናቸው፣ ነገር ግን፣ ዛሬ እኛ ስናነባቸው፣ ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት ለእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ዓላማ እነዚህን ቃሎች ለመንፈሳችን ይናገሩናል፤ በእያንዳንዱ መልእክት መጀመሪያ ላይ ያለው የጌታ ቃል ለአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ነው፣ በሁሉም ዘመናት ያሉ ሰዎች ሲያነቡት ግን ለሁሉም አብያተ ክርስቲያናት የሆነ የመንፈስ ንግግር ይሆናል።

ሠ. የመንፈስ ንግግር ሁልጊዜም ወደ ክርስቶስ መስረጽ ውስጥ ያዘረናል፤ የመንፈስ ንግግር የክርስቶስ መስረጽ ነው—ተዛ. 2 ቆሮ. 3፥16-18፡-

1. ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት ለአብያተ ክርስቲያናት የሚገሩትን ንግግር በምንሰማበት ጊዜ ሁሉ፣ በሚቀይረን፣ በልውጠት በሚለውጠን፣ ተገቢ የግንባታ ዕቃ በሚያደርገንና ወደ እግዚአብሔር ግንባታ ውስጥ በሚገነባን ከቡር፣ ጣፋጭና ውድ በሆነ መተላለፍ፣ መስረጽ ሥር ወዲያውኑ እንሆናለን።
2. ወደ እሳት ባሕር መሄድ ያለበት ማንኛውም ነገር በሰባቱ መብራቶች ይቃጠላል (ራእ. 4፥5)፣ እኛም አሁን የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ክፍሎች እንሆን ዘንድ ክርስቶስ በሆነው ሁሉ እየተሰረጽን በሰባቱ ዓይኖች ሥር ነን (5፥6)።

ረ. ምንም እንኳን አማኞች የመንፈስን ንግግር ሊሰሙ የሚችሉበት ሥፍራ ላይ ቢሆኑም፣ ከዚህም የተነሣ በቀላሉ ሊሰሙ የሚችሉ ጆሮዎች ቢኖራቸውም፣ ሁላቸውም ንግግሩን በቅርበት አይከታተሉትም፤ በመሆኑም፣ ለድል ነሺዎች ጥሪ አለ።

ሰ. መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚናገረውን ለመስማት ጆሮ ያላቸው መስማት አለባቸው፣ የሚሰሙትም ድል ነሺዎች ይሆናሉ፡-

1. በኢኮኖሚው መሠረት ነገሮችን እንድናይ ድምፁን እንሰማው ዘንድ ጌታ ሁልጊዜ ጆሮዎቻችንን ሊከፍት ይፈልጋል—ኢዮብ 33፥14-16፤ ኢሳ. 50፥4-5፣ ዘጸ. 21፥6።
2. የከበዱ ጆሮዎች መገረዝ ያስፈልጋቸዋል—ኤር. 6፥10፤ ሐዋ. 7፥51።
3. የኃጢአተኞች ጆሮ በሚቤዠው ደም መንጻትና በመንፈስ መቀባት ያስፈልገዋል—ዘሌ. 14፥14፣ 17፣ 28።
4. ጌታን እንደ ካህናት ለማገልገል፣ ጆሮዎቻችን በሚቤዠው ደም ሊነጹ ይገባል—ዘጸ. 29፥20፤ ዘሌ. 8፥23-24።
5. መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት እየተናገረ ሳለ፣ እኛ ሁላችን የመንፈስን ንግግር እንሰማ ዘንድ የተከፈተ፣ የተገረዘ፣ የነጻና የተቀባ ጆሮ ያስፈልገናል።

ሸ. የመንፈስ ንግግር በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ስላሉት ስለ ሰባቱ ዓይነት አብያተ ክርስቲያናት ነው፡- የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን (ኤፌሶን)፣ መከራ የምትቀበለው ቤተ ክርስቲያን (ሰምርኔስ)፣ ዓለማዊዋ ቤተ

ክርስቲያን (ጴርጋሞን)፣ ከሃዲዋ ቤተ ክርስቲያን (ትያጥሮን)፣ የታደሰችው ቤተ ክርስቲያን (ሰርዴስ)፣ የተመለሰችው ቤተ ክርስቲያን (ፊልድልፍያ) እና ከተመለሰች በኋላ የዘቀጠችው ቤተ ክርስቲያን (ሎዶቅያ) ናቸው:-

1. የመጨረሻዎቹ አራት ዓይነት አብያተ ክርስቲያናት ጌታ ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ ይቆያሉ።
2. ያለ ጥርጥር፣ የተመለሰችው ቤተ ክርስቲያን ብቻ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ ዓላማ መፈጸም ትችላለች፤ ጌታ የሚፈልገውም እርሷን ብቻ ነው፤ የጌታን ምርጫ መውሰድ አለብን።
3. ሎዶቅያ ለብታ እና መንፈሳዊ ትምክህት ያለባት የተዛባች ፊልድልፍያ ናት—ራእ. 3፥14-17:-
   ሀ. ሎዶቅያ ማለት ሁሉንም ነገር ማወቅ በእውነታው ግን ስለ ምንም ነገር አለመቀጣጠል ነው፤ በስም ሁሉ ነገር አለው፣ ነገር ግን ስለ ምንም ነገር ግን ሕይወቱን መሠዋት አይችልም፤ የቀደመውን ክብሩን ያስታውሳል፣ አሁን በእግዚአብሔር ፊት ያለውን ሁኔታ ግን ይረሳል።
   ለ. በፊልድልፍያ መንገድ ላይ መቀጠል ከፈለግን፣ በእግዚአብሔር ፊት ራሳችንን ማዋረድን ማስታወስ አለብን—ተዛ. ቁ. 7-22፣ ኢሳ. 57፥15፤ 66፥1-2።

## II. በተመለሰችው ቤተ ክርስቲያን (በፊልድልፍያ)፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ቤት (ለእግዚአብሔር መንግሥት ግንባታ በሆነው የዳዊት ቤት የተመሰለው) (የግምጃው ቤት) ቁልፍ በጫንቃው ላይ እንዳለው ማንነት ይታያል—22፥22፤ ራእ. 3፥7:-

ሀ. ለተመለሰችው ቤተ ክርስቲያን፣ ክርስቶስ ከመክፈትና ከመዝጋት ሥልጣን ጋር የዳዊት ቁልፍ፣ የመንግሥቱ ቁልፍ ያለው ነው፤ ጌታ በአንድ ልብ ለሆነችው ለተመለሰችው ቤተ ክርስቲያን ማንም ሊዘጋው የማይችለውን የተከፈተ በር ሰጥቷል—ቁ. 8፣ ተዛ. መዝ. 133።

ለ. ወደ ነጭ ድንጋይ እንድንለወጥና የእግዚአብሔር ስም፣ የኢዲሲቱ ኢየሩሳሌም ስምና አዲሱ የጌታ ስም ያለበት ዓምድ ሆነን ወደ እግዚአብሔር ቤት ውስጥ እንድንገነባ የዳዊት ቁልፍ በሩን ይከፍትልናል—ራእ. 2፥17፣ 3፥12።

1. ለእኛ ወደ እግዚአብሔር ውስጥ መገንባት፣ የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ክፍል መሆንና የአዲሱ ክርስቶስ ክፍል መሆን በሰው ዘንድ የማይቻል ነው፤ ነገር ግን በውስጣችን ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ አለመቻልን የሚያስወግድ ንጥረ ነገር በውስጡ ይዟል—ሮሜ 8፥2፤ ራእ. 3፥7-13፤ ተዛ. ዘፍ. 28፥12-19፤ ዮሐ. 1፥51።
2. የእግዚአብሔር ብልጥግናዎች በክርስቶስ ለድሰታችን ያሉበትን የእግዚአብሔር ግምጃ ቤት በር ለመቆጣጠር ክርስቶስ ቁልፉ አለው፤ እነዚህን ብልጥግናዎች ለእኛ መክፈቱንም መዝጋቱንም ተለማምደነዋል—ኤፌ. 4፥30፤ 1 ተሰ. 5፥17፤ 1 ዮሐ. 1፥7፣ 9:-
   ሀ. ብልጥግናዎቹን እንደ ውድ ነገር ለመደሰት፣ በመንፈስ ድሆች እና ልበ ንጹሐን እንሆን ዘንድ በሕይወት ስሜት መሠረት ከጌታ ጋር ተገናኝተን በመቆየት ከጌታ ጋር በመገናኘት መዝለቅ ያስፈልገናል—2 ቆሮ. 2፥10፤ ሮሜ 8፥6፤ 10፥12-13፤ ቆላ. 3፥16፤ ማቴ. 5፥3፣ 8።
   ለ. ብልጥግናዎቹን እንደ መዝገብ ለመደሰት፣ መስቀሉን በመሸከምና የነፍስ ሕይወትን በማጣት እኔነትን የመካድ ቁልፎችን ማንቀሳቀስ መማር ያስፈልገናል፤ ክርስቶስ በእኛ ውስጥና ለእኛ ሁሉንም ነገር እንዲሆን፣ በእኛ በኩልና ስለ እኛ ሁሉን እንዲያደርግ ሁላችንም መወገድ አና በክርስቶስ መተካት ያለብን "ሳምናሶች" ነን—ኢሳ. 22፥15-19፤ ማቴ. 16፥24-25።

## III. ከተመለሰች በኋላ በዘቀጠችው ቤተ ክርስቲያን፣ ክርስቶስ ከድል ነሺዎቹ ጋር እራት እንደሚበላው ማንነት እና እርሱ ድል ነሥቶ ከአባቱ ጋር በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጠው፣ ድል ነሺዎቹም ከእርሱ ጋር በዙፋኑ ላይ ይቀመጡ ዘንድ እንደሚሰጣቸው ማንነት ይታያል—ራእ. 3፥20-21:-

ሀ. "እነሆ [በበር] ቆሜ አንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ [በሩንም] ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት አበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል"—ቁ. 20:-

1. በሩ የግለሰቦች ልብ ሳይሆን የቤተ ክርስቲያን በር ነው፤ ጌታ እንደ የቤተ ክርስቲያን ራስ የዘቀጠችውን ቤተ ክርስቲያን በር እያንኳኳ በውጭ ቆሟል።
2. በሩ የቤተ ክርስቲያን በር ነው፣ ሆኖም በሩ የሚከፈተው በግለሰብ አማኞች ነው፤ በሎዶቅያ ያለችው ቤተ ክርስቲያን እውቀት አላት፣ የጌታ መገኘት ግን የላትም።
3. በጌታ ዓይኖች ከተመለሰች በኋላ የዘቀጠችው ቤተ ክርስቲያን (1) በከንቱ የአስተምህሮ እውቀት ባለጠጋ በመሆን ትምክህተኛ ስለሆነች በእውነታው ግን በክርስቶስ ብልጥግናዎች ልምምድ እጅግ ድሀ ስለሆነች ጎስቋላ ናት፤ (2) የተራቆተች፣ ዕውርና ኃፍረትና ጨለማ የሞላባት ስለሆነች ምስኪን ናት፤ (3) በክርስቶስ

ልምምድ እና በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መንፈሳዊ እውነታ ድሀ ስለሆነች ድሀ ናት፤ (4) በእውነተኛ መንፈሳዊ ነገሮች ጥልቅ የሆነ ውስጣዊ እይታ ስለሌላት ዕውር ናት፤ (5) በክርስቶስ ስለማትኖር ወይም በየዕለት ምልልሷ እንደ ሁለተኛው ልብስ እንደ ውስጠ ልምምዳዊ ጽድቋ ክርስቶስን ስለማትኖር የተራቆተች ናት—ቁ. 15-17፣ ተዛ. መዝ. 45፥1፣ 9-14።

4. ጌታ መላዋን ቤተ ክርስቲያን እያደበ ነው፣ የጌታን ማደብ መቀበል ግን ግላዊና ውስጠ ልምምዳዊ ጉዳይ መሆን አለበት።
5. ከጌታ ጋር እራት መብላት አንድ የምግብ ዓይነት ብቻ መብላት ብቻ ሳይሆን ከምግብ ብልጥግናዎች፣ ከግብዣ መካፈል ነው፤ የእስራኤል ልጆች የመልካሚቱን ምድር የከነዓንን ብልጡግ ፍሬ የመብላታቸውን ምሳሌ ፍጻሜ ይህ ሊያመለክት ይችላል—ኢያሱ 5፥10-12።
6. ክርስቶስን እንደ ሕይወት ዛፍ፣ እንደ ተሰወረው መና እና እንደ ግብዣው በመደሰታችን በኩል እርሱን እንደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም እንገልጠው ዘንድ በቅንብራችን ከእርሱ ጋር እንደ አንድ አካል እንዋሐዳለን—ራእ. 2፥7፣ 17፤ 3፥20።

ለ. “እኔ ደግሞ ድል እንደነሣሁ ከአባቴም ጋር በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጥሁ፥ ድል ለነሣው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ—ቁ. 21፦

1. ድል የነሣው በጌታ ሥልጣን ይካፈል ዘንድና በሚመጣው የሺህ ዓመት መንግሥት ጌታ በምድር ሁሉ ላይ ሲገዛ አብሮ ነጋሽ ይሆን ዘንድ፣ ከጌታ ጋር በዙፋኑ ላይ መቀመጥ ሽልማቱ ይሆንለታል—ሉቃ. 19፥11-27፤ ማቴ. 25፥21፣ 23።
2. የእግዚአብሔር ውጥን ሰው በዙፋኑ ላይ ይሆን ዘንድ ራሱን ወደ ሰው ውስጥ መሥራትና በሰው ላይ መሥራት ነው፤ መሻቱ እኛን የዙፋኑ ሕዝብ ማድረግ ነው—ራእ. 2፥26-27፤ 3፥21፤ 22፥5፤ ተዛ. ኢሳ. 14፥12-14።
3. ጌታ ኢየሱስ በስቅላቱ፣ በትንሣኤውና በዕርገቱ ወደ ዙፋኑ እንዲመጣ ተደርጓል፤ ስሙ ኢየሱስ የሆነ እውነተኛ ሰው በዙፋኑ ላይ ነው (ሕዝ. 1፥26)፤ አሁን፣ ዛሬ የሰማይና የምድር ጌታ፣ የአጽናፍ ዓለም ጌታ ሰው ነው፤ “ኢየሱስ ጌታ ነው” ብለን የምናውጀው ለዚህ ነው፣ “ኦ ጌታ ኢየሱስ” ብለን የምንጠራውም ለዚህ ነው።
4. ጌታ ኢየሱስ ወደ ዙፋኑ በሚወስደው መንገድ ቀዳሚ ሆኖ መራ፤ እርሱ ወደ ዙፋኑ የሚወስደውን መንገድ የቀደደው ፈር ቀዳጁ፣ ቀዳሚው ነው (ዕብ. 6፥20፤ 2፥6-9)፤ መንገዱን ቀዶታል፣ እንከተለውም ዘንድ ቅድሚያውን ወስዷል (ቁ. 10-12)።
5. እግዚአብሔር ወደ ክብር ሊያስገባንና በዙፋኑ ላይ ሊያደርገን ስለ ወጠነ አሁን ወደ ዙፋኑ በፍጥነትና በቁርጠኝነት እያመራን ነው፤ እግዚአብሔር ራሱን በሰው በኩል መግለጥ ይሻል፣ በሰው በኩል መግዛት፣ ማስተዳደርም ይሻል፤ የእግዚአብሔር ውጥን ሰይጣንን መጣልና በሰይጣን የተማረኩ ብዙዎችን ዋጅቶ ወደ ዙፋኑ ማምጣት ነው።
6. የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን ተጠርተናል፣ ነገሥታት ለመሆንም ተወስነናል፣ ነገር ግን ለንግሥና ብቁ ያደርገን ዘንድ እግዚአብሔር በውስጣችን ሊሠራና በእኛ ላይ ሊሠራ ያስፈልገናል—ሮሜ 5፥17፣ 21፤ ተዛ. ሕዝ. 1፥22፣ 26፤ ማቴ. 8፥9።

*© 2025 Living Stream Ministry*